# መድረክና ምህዋሩን የሳተው የዴሞክራሲ እይታው

ሰለሞን አጎናፍር- ከአዲስ አበባ

ወቅቱ ያለፈው የ2002 ዓ.ም አጠቃላይ አገር አቀፍ ምርጫ የመራጮች ድምፅ የመስጠት ሂደት ሊከወን ጥቂት ቀናት የቀረበት ጊዜ ነበር፡፡በዚህ ጊዜ ታድያ ከመድረክ ከፍተኛ አመራሮች መካከል አንዱ ከአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣናት በተደረገለኝ ግብዣ በሚል ወደ አሜሪካ ለጉብኝት ያቀናሉ፡፡

እኝሁ የመድረክ ከፍተኛ አመራር ወደ ዋሺንግተን ዲሲ በተያዘላቸው ፕሮግራም መሰረት ደርሰው ከአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በኢትዮጵያ አገር ዓቀፉን ምርጫን ጨምሮ በአጠቃላይ በዴሞክራሲ ስርአቱ ላይ "ይታያሉ" ባሏቸው እንከኖች ላይ መምከራቸውን የተለያዩ የግል ጋዜጦች በዘገባቸው ይፋ አድርገውት ነበር፡፡

ሆኖም አንድ የግል ጋዜጣ ግን ከውስጥ አዋቂ ምንጭ አገኘሁት በሚል ይህንን አስመልክቶ ያወጣው ዜና በርካታ ኢትዮጵያውያንን ያስገረመ ነበር፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ የ2002 ዓ.ም አገር አቀፉ ምርጫ ሲቃረብ በተደረገልኝ ግብዣ ወደ ዋሺንግተን ዲሲ አቀናሁ ያሉት የመድረኩ ከፍተኛ አመራር ከአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ባደረጉት ውይይት ወቅት ያቀረቡት ዋነኛው አጀንዳና ጥያቄ ***"በአገር አቀፉ የ2002 ዓ.ም ምርጫ እንሳተፍ ወይስ አንሳተፍ ምን ትመክሩናላችሁ?"*** የሚል እንደነበር አመልክቷል፡፡

የአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣናትም ለዚህ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ መድረክ **በዚህ ምርጫ ላይ ተሳታፊ ሊሆን እንደሚገባው** በአፅንኦት እንዳሳሰቧቸው ነበር የጋዜጣው ዘገባ የጠቆመው፡፡

የመድረክ ባለስልጣናትም በምርጫው እንዲሳተፉ ከአሜሪካ ከፍተኛ ባለስልጣናት ባገኙት ይሁንታ መሰረት ይሁን በራሳቸው ፈቃድ ባልታወቀ ሁኔታ የሁዋላ ሁዋላ የምርጫውን ሂደት ሲያንቋሽሹና ሲያጣልሉበት ከነበሩበት ሁኔታ ወጥተው የሂደቱ ተሳታፊ ሊሆኑ ችለዋል፡፡

ሆኖም መድረክ በዚህ አገር አቀፍ ምርጫ ያገኘው አጠቃላይ የህዝብ ድምፅ ውጤት አመራሮቹ "ሰፊ የህዝብ ድጋፍ" እንዳላቸው ሲገልፁ የቆዩበት ሁኔታ ከተጨባጭ እውነታው ጋር የማይገናኝ **"ፍዬል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ"** እንደሚሉት አይነት እንደነበረ የተረጋገጠበትሆኖ አለፈ፡፡

ከትናንቱ ሂደት ለዛሬ ትምህርት በመቅሰም ራሳቸውን ለመለወጥና ለማሻሻል ያልታደሉት የመድረክ አመራሮች ግን በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ወሳኝ የሆነውን ህዝብ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታውም ሆነ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ዋነኛ ተሳታፊ ከማድረግ ይልቅ ዛሬም የውጭ ጣልቃ ገብነትን በአገራቸው ጉዳይ ላይ ሲማፀኑ መታየታቸው እጅግ አሳፋሪ ነው፡፡

የመድረክ ከፍተኛ አመራሮች ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ በሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደት ላይ ከእንግሊዝ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር እንዳካሄዱ የተጠቀሰው ውይይት ቀደም ሲል ለተጠቀሰው አባባል ግልፅ ማሳያ ነው፡፡

የመድረክ አመራሮች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ ለበርካታና ተደጋጋሚ ጊዜያት የምእራባውያን መንግስታትን ጣልቃ እንዲገቡ ሲጋብዙ ይስተዋላሉ፡፡ይህም በእርግጥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በውጭ ሃይሎች ጫና የሚጎለብት ነውን? የሚለውን ጥያቄ እንዳነሳ አስገድዶኛል፡፡

ለዚህ አባባሌ በአስረጂነት የምጠቅሰው ዊኪሊክስ የተሰኘው ድረ ገፅ ባለፈው አመት ይፋ ያደረገውን መረጃ ነው፡፡እንደ ዊኪሊኪስ መረጃ ከሆነ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት እኤአ የ2010 የአገር አቀፉ ምርጫ ቅስቀሳ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ከመድረክ አመራሮች አንዱ የሆኑት ዶክተር መራራ ጉዲና ከትግል አጋሮቻቸው ጋር ለውይይት ተገኝተው ነበር፡፡

በዚሁ ወቅት ታድያ ዶክተር መራራ የአሜሪካ ባለስልጣናትን ለመሆኑ "**የአሜሪካ መንግስትና አስተዳደር በኢትዮጵያ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መብቶች እንዲከበሩ ያለው ቁርጠኝነት ምን ያህል ነው?**" ሲሉ መሞገታቸውን ድረ ገፁ አስፍሯል፡፡

ዶክተሩ አያይዘውም በአሜሪካ የኦባማ አስተዳደር በአዲስ ስልጣን መያዙን ተከትሎ በኢትዮጵያ በርካታ ተቃዋሚዎች "**አሜሪካ የኢህአዴግ አስተዳደር ላይ ይፋዊ ወቀሳ ከመሰንዘር የተቆጠበችበትን የቀደመው ሁኔታ እንደሚስተካከልና ለኢትዮጵያ የምትሰጠውን ጭፍን ድጋፍም እንደምታቆም ተስፋ አድርገው የነበረ ቢሆንም ይህ ግን ተግባራዊ አልሆነም**" ሲሉ በቁጭት መናገራቸውንም ይህው መረጃ ግልፅ አድርጓል፡፡

በዚህ ውይይት ላይ ተሳታፊ የነበሩ ቱባ ቱባ የተቃዋሚ አመራሮችና የዶክተር መራራ የትግል ጓዶችም እርሳቸው በሰነዘሩት ሃሳብ በመስማማት የኤምባሲው ባለስልጣናት የአሜሪካ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ባለው ግኑኝነት ላይ ለምን ለውጥ እንዳላደረገ መልስ እንዲሰጡበት አፋጠዋቸው ነበር ብሏል ዊኪሊክስ፡

ይህን ሳነብ ታድያ በአንድ አገር የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው ሂደት የሚጎለብተው እንዴትና በማን ነው? የሚል ጥያቄ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ለሆኑት ለዶክተር መራራ ልሰነዝር ወደድሁ፡፡እንደ እርሳቸው በፖለቲካ ሳይንስ ዘርፍ የካበተ ልምድ አለኝና በርካታ መፅሃፍትን አንብቤያለሁ የሚል አንድ ምሁር አሜሪካ ከራሷ አገር አልፋ እንዴትና በምን ሂሳብ በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ መጎልበት ተጠያቂ እንደምትሆን? ግልፅ ቢያደርጉልን በተገባ ነበር፡፡

እኝህ በፖለቲካውም ሆነ በአካዳሚክ ትምህርት የካበተ ልምድ አለኝ የሚሉና ህዝቡን ወክለው በተቃውሞው ጎራ የተሰለፉ አመራር እስከ መቼስ ይህን መሰል የውጭ ጣልቃ ገብነት እየጠየቁ በአገርና በህዝብ ሉአላዊነትና ነፃነት ላይ እንደሚሳለቁም ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ፈፅሞ ግልፅ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያን ህዝብ በአገሩ ጉዳይ ላይ እንደባይተዋር የሚቆጥርና አስተዋፅኦውን በማሳነስ የሚዘባበትበት ምሁር ነኝ ባይ "የኢትዮጵያን ህዝብ እወክላለሁ" በሚል በተለያዩ የውጭ አገራት ኤምባሲዎች ደጅ ሲጠና መታየቱ ህሊና ላለው ሰው ከዚህ በላይ አገርንና ወገንን የሚያሳፍር እጅግ የወረደና አሳፋሪ ድርጊት የለም፡፡

ዳሩ ምን ያደርጋል የኒዮ ሊበራሉን ሃይል አላማ በአገራቸው ላይ ተፈፃሚ ለማድረግ ሳይታክቱ በጉዳይ ፈፃሚነትና በተላላኪነት ላይ ታች ከማለት በስተቀር ሌላ ለወገን አኩሪ የሆነ ተግባር አንዳች መልካም

ተግባር ሲፈፅሙ ለመታዬት ያልታደሉት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ውኋቸውን የሚያሳልፉት በየኤምባሲዎች ደጆችና ቢሮዎች ከሆነ አመታት አስቆጥረዋል፡፡

እነዚህን ሃይሎች ይህን መሰል የአገራቸውን ሉአላዊነትና ነፃነት አሳልፎ የሚሰጥ ተግባር መፈፀማቸውን በእነርሱ ምልከታ "ዴሞክራሲን ማስፈን" በሚል ከተግባሩ ጋር የሰማይና የምድር ያህል የተራራቀ ትርጓሜ ከተሰጠው ቆይቷል፡፡

"ኢህአዴግ የሚናገር ምላስ እንጂ የሚሰማ ጆሮ የለውም" በሚል ራሳቸውን እንጂ ድርጅቱን በማይገለፀው አጉል ፈሊጣቸው የሚታወቁት "ምሁር" ነኝ ባዩ ዶክተር መራራ የሚሰማ ጆሮ ካላቸው የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪክ የሚያውቀው በሉአላዊ አገሩ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ሊገቡ የሞከሩ የውጭ ሃይሎችን አሳፍሮ ሲመልስ ነው፡፡

ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ቀደም ሲል የአገራቸውን ሉአላዊነትና ነፃነት ሊደፍሩ የሞከሩ ቅኝ ገዥዎች ላይ የወሰዱት አኩሪ የጀግንነት እርምጃም የጥቁር አፍሪካውያን የአልደፈር ባይነት ተምሳሌት እንዳደረጋቸው ላስታውሰዎት እወዳለሁ፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የመድረክ አመራሮች በአዲስ አበባ በተለያዩ የምእራባውያን ኤምባሲዎችና በአንዳንድ የአውሮፓ አገራትና በአሜሪካ እየተገኙ በአገሪቱ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የውጭ ሃይላት ተፅእኖ እንዲያሳርፉ መጠየቃቸው ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝን በአገሪቱ ለማስፈን እየጣሩ መሆናቸውን ከማረጋገጡ ባሻገር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ሊሆን አይችልም፡፡

እንደሚታወቀው በአለም ላይ ያሉ የተለያዩ አገራት የሁለትዮሽ የወዳጅነት ግኑኝነት የሚመሰርቱት አገራቱ የየራሳቸውን ሉአላዊነታቸውና ነፃነታቸውን ባስከበረ መልኩ ነው፡፡ አንደኛው አገር በሌላኛው አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በማይገባበት ሁኔታ፡፡

ይሁን እንጂ አገራት ሉአላዊነታቸውና ነፃነታቸውን ባስከበረና ከውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ የሚመሰርቱት የሁለትዮሽ የወዳጅነት ግኑኝነት በማህበራዊ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ መስክ በጋራ ጥቅምና መከባበር መርህ ላይ የተመሰረተ ትብብር እንዲያደርጉ ግን ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክትላቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ምክንያቱም ይህን መሰል ትብብር የወዳጅነት ግኑኝነት ለሚመሰርቱት ሁለቱ አገራት መንግስታትም ሆነ ህዝቦቻቸው የሚያስገኘው ጥቅም ከፍተኛ ነውና፡፡አንዱ አገር በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በማይገባበት ሁኔታ የሚካሄደው ይህው የሁለትዮሽም ሆነ ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው አገራት ጋር በጋራ የሚመሰረተው የግኑኝነት ማእቀፍም መርሁ በመተማመንና በመከባበር ላይ እንዲካሄድ የሚያስችል የህግ ማእቀፍ ያለው ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በአንድ ነፃና ሉአላዊ አገር ውስጥ የሚካሄድ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ወሳኙና ዋነኛ ተዋናዩና ተሳታፊው የዚያ አገር ህዝብና መንግስት ብቻ መሆናቸው በአለም ዓቀፍ የፖለቲካ ሳይንስ መርህም ሆነ በአለም ዓቀፍ ህግ ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡

**በአንድ አገር የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታን እውን ማድረግ ማለት የህዝብ አስተዳደርን ተሳትፎን በሰፊው ማስፈን ማለት** ነው፡፡ይህ እንደመሆኑ የአንድ አገር **ዜጎች በሉአላዊና በነፃ አገራቸው ያለ ማንም**

ጣልቃ ገብነት በአገራቸው በሚካሄዱ ዘርፈ ብዙ የልማት የመልካም አስተዳደር ግንባታም ሆነ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች ውስጥ ዋነኛ ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ አገራት የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጡት ተግባር ነው፡፡

የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታን እውን ባደረጉ አገራት በአገራቸው በሁሉም ዘርፍ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የአብላጫው ዜጎች ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆንበት ስርአት እንደሚፈጠር አብዛኛው የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

ይህም በመሆኑ በአንድ አገር የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታን በተሳትፏቸው የሚያጎለብቱትም ሆነ የሚያሳድጉት የስርአቱ ባለቤት የሆኑት የአገሪቱ ዜጎች እንጅ ሌላ የውጭ ሃይል ሊሆን አይችልም፡፡

በመሆኑም በአለም ላይ በውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት ዴሞክራሲን የገነባ ወይም ያዳበረ አገር የሌለ ከመሆኑም በላይ በአገራት ታሪክ ህዝቦች ለዴሞክራሲ የሚያደርጉት ትግል ውጤታማ የሚሆነው በራሳቸው በህዝቦች ተሳትፎ የተገነባ ሲሆን ብቻ እንደሆነ በዚህ ዘርፍ የተካሄዱ የምሁራን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

በአለም ላይ ያለ ማንም የውጭ ጣልቃ ገብነት ነፃነታቸውንና ሉአላዊነታቸወን ባስጠበቀ መልኩ የዴሞክራሲ ስርአትን የሚገነቡ አገራት ሰላማዊና የተረጋጉ ሆነው የኢኮኖሚ እድገታቸውን ባረጋገጡ ሁኔታ በፍጥነት ወደ ብልፅግና እንደሚያመሩ በተጨባጭ የተረጋገጠ ነው፡

ከዚህ በተፃራሪው ግን በሉአላዊ አገራት ላይ የውጭ ሃይሎች የዜጎችን ሚና ተክተው “ዴሞክራሲ እናሰፍናለን” በሚል ጣልቃ ሲገቡ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ሊገነቡ ይቅርና በማያባራ ጦርነትና ግጭት ውስጥ ተዘፍቀው ለውድመት ይዳረጋሉ፡፡ ለዚህም እንደ አብነት ኢራቅና አፍጋኒስታን ይጠቀሳሉ፡፡

አፍጋኒስታንንና ኢራቅ ዛሬ ያሉበት ሁኔታ በአንድ ሉአላዊና ነፃ አገር ላይ በውጭ ሃይሎች በጣልቃ ገብነት የሚገነባ ዴሞክራሲና የሚሰፍን ሰላም እንደሌለ በገሃድ ያረጋገጠ ነው፡፡

በተጨማሪም በአፍጋኒስታንንና ኢራቅ በውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት የተፈጠረው የተመሰቃቀለ ሁኔታ በሉአላዊና ነፃ አገራት የፖለቲካና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጉዳይ የመላው የአገሪቱ ዜጎች ተሳትፎ ብቻ እውን እንደሚሆን ለአለም ህዝብ ትምህርት የሰጠ ነው ፡፡

ወደ አገራችን ተጨባጭ እውነታ ስንመጣ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስት የበርካታ ብሄር ብሄረሰቦች በሆነችው አገር ሰላምና መረጋጋት በማሰፍን ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማስመዘገብ አገሪቱን ከነበረችበት ስር የሰደደ ድህነት የማውጣት ጉዳይን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ያለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ልማትን ማፋጠንና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማስመዘገብ እንደማይቻል በከፍተኛ ሁኔታ የሚያምነው የኢትዮጵያ መንግስት ለዚሁ ተግባራዊነት በቁርጠኝነት የተንቀሳቀሰው በውጭ ሃይሎች ባገኘው ምክር ታግዞ አልነበረም፡፡

መንግስት የኢትዮጵያን ህዝቦች ከነበሩበት ስር የሰደደ ድህነት በማላቀቅ በአሁኑ ወቅት ሰላማዊና የተረጋጋች አገር መገንባትና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ የቻለውም ከውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት በፀዳ መልኩ ዜጎች በአገራቸው በሚካሄዱ ዘርፍ ብዙ እንቅስቃሴዎች ዋነኛና ብቸኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማስቻሉ ነው፡፡

ይህንንም እውን ያደረገው ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ብቻ የተገናዘበ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር ነድፎ ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት የሚመራበት የልማታዊና የዴሞክራሲያዊ ስርአት መርህ የምእራባውያንም ሆነ የሌሎች የውጭ ሃይሎችን ጫና የሚያስተናግድበት አንዳችም ክፍተት የሌለው መሆኑን እነ ዶክተር መራራ ሊገነዘቡ አልቻሉም፡፡ አሊያም አልፈለጉም፡፡

ይህም በመሆኑ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ዛሬም እንደ ትናንቱ በየምእራብ አገራት ኤምባሲ ደጃፍና ቢሮዎች እየተኮለኮሉ "ዴሞክራሲ አስፍኑልንና ጣልቃ ግቡልን" በሚል ማላዘናቸውን እንደቀጠሉበት ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መንግስት ግን በአገሪቱ የዴሞክራሲዊ ስርአት ግንባታ በልማቱም ሆነ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች የሚያካሂዳቸውን ተግባራት  የምእራባውያንን ውግዘትና ጫና በመፍራት ሳይከውናቸው አሊያም ሳይፈፅማቸው የቀረበት ሁኔታ እስካሁን ባሉት አመታት አልታዬም፡፡

ሆኖም እያዩ የማይመለከቱትና እየሰሙ የማያዳምጡት እነ ዶክተር መራራ ግን የተቃዋሚ ፓርቲ መስርተው መምራት ከጀመሩበት ጊዜ እስካሁን ድረስ  የምእራባውያን መንግስታት በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የተለያዩ እርምጃዎችን እንዲወስድና ጫናዎችን እንዲያሳርፍ ያልተማፀኑበት ጊዜ ኖሮ አያውቅም፡፡

በየጊዜው የሚለዋወጡት የተለያዩ የአሜሪካ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ግን ኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ሉአላዊነት ብሄራዊ ጥቅምና እንዲሁም በህዝቦች ነፃነት ላይ የሚመጣን የማንኛውም ምእራባዊም ሆነ የውጭ ሃይል መመሪያም ሆነ ትእዛዝ  እንደማይቀበልም እንደማይተገብርም ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡

እነ ዶክተር መራራ ይህን መገንዘብ እንዲቻላቸውም ዊኪሊክስ በድረ ገፁ ላይ የዛሬ አንድ አመት አካባቢ ይፋ ያደረገውን መረጃ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በዊኪሊክስ ድረ ገፅ ላይ የሰፈረው መረጃ በኢትዮጵያ ከ1997 ምርጫ መጠናቀቅ በሁዋላ ከአምባሳደር ቪኪ ሃደልስተን ቀጥሎ የአሜሪካ አምባሳደር ሆነው ዶናልድ ያማማቶ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን ይጠቅሳል፡፡

አምባሳደሩ ከአገራቸው ከአሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት አሜሪካውያን በሚልኩትና በሚሰጡት ትእዛዝ እንደሚንቀሳቀስ አድርገው የተሳሳተ ግንዛቤ ይዘው እንደነበር በድረ ገፁ ከሰፈረው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

አምባሳደሩ ታድያ ይህ ሁኔታ ባሳደረባቸው ተፅእኖ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስን ጨምሮ ከተለያዩ የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በአንዳንድ ርእሰ ጉዳዮች ላይ በሚያካሂዱት ውይይት መግባባት ላይ መድረስ ተስኗቸው እንደነበርም ይጠቁማል፡፡

ይህም የሆነው አምባሳደር ያማማቶ ከአሜሪካ ወደ አዲስ አበባ በመጡባቸው የመጀመሪያዎቹ ወራት የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ የምርጫ ሂደት የኢትዮጵያውያን ዜጎች ጉዳይ ሆኖ ሳለ በአገሪቱ ውስጥ

የፖለቲካ ሂደት ጣልቃ የገቡ የአይአርአይ (International Republican Institute) የኤንዲአይ( National Democratic Institute) እንዲሁም አይ ኤፍ ኢ ኤስ (International Foundation for Electoral Systems) አባላትን በማባረሩ ነው፡፡

አምባሳደር ያማማቶ የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን አባላት በማባረሩ እጅግ መባሳጨታቸውን ለአሜሪካ ባለስልጣናት በፃፉት ደብዳቤ ላይ "ከሀያ አመት ወዲህ በማንም አገር ያልተሞከረ ድፍረት" ሲሉ ያስተላለፉት መልእክት ያመላክታል፡፡

የአምባሳደሩን ብስጭት ያባባሰው ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን የውጭ ዜጎች ማባራሩ ብቻ ሳይሆን የተባረሩት የልኡካን ቡድን አባላት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ  አሜሪካ ላቀረበችው ጥያቄ የሰጠችው ምላሽ አሻፈረኝ የሚል መሆኑ ነው፡፡

ይህንና መሰል የሆኑ በተለይም ከምርጫ 1997 ዓ.ም መጠናቀቅ በሁዋላ የአሜሪካ መንግስት በየጊዜው ስልጠናን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች በኢትዮጵያ ሊፈፅማቸው ያቀዳቸውን ተግባራት የኢትዮጵያ መንግስት አመራሮች ጠቀሚታውን ስላላመኑበት ለበርካታ ጊዜያት ውድቅ አድርገውበታል፡፡

ይህና መሰል የኢትዮጵያ መንግስት ተደራራቢ ውሳኔዎች አምባሳደር ያማማቶን እያስቆጣቸው ቢሆንም ድርጊቱ ግን ቀደም ሲል በተጠቀሱት መስኮች ብቻ የሚያቆም አልሆነም፡፡

እንደ ዊኪሊክስ መረጃ የአሜሪካ መንግስት በተለይም በ1999 ዓ.ም በኢትዮጵያ ለገዥው ፓርቲ ሃላፊዎች ያቀረበላቸውን የፊቃደኛ ነብኝዎች ፕሮግራም ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም ይላል፡፡የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ከተሰጡት 41 የስልጠና ድጋፍ እድሎች 29ኙን አልቀበልም ማለቱን ይገልፃል፡፡

yCombined Joint Task Force- Horn of Africa (GJTF-HoA እንዳይካሄድ የኢትዮጵያ መንግስት ከመከልከሉም በላይ የአሜሪካ የፀረ ሽብር አሰልጣኞች የወሰን ፀጥታ አሰልጣኞች ከብላቴ ማባረሩም በድረ ገፁም ተጠቅሷል፡፡

የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ፍላጎት ያሳደረባቸውን የግኑኝነት መስኮች የኢትዮጵያ መንግስት በድፍረት ውድቅ ማድረጉ ያበሳጫቸው አምባሳደር ያማማቶ በወቅቱ የአሜሪካ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ባለው ግኑኝነቱ ላይ "የቅኝት ለውጥ" እንዲያደርግ እስከ መጠቆም መድረሳቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

ሆኖም አምባሳደር ያማማቶ የኢትዮጵያ ቆይታቸው እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ግን በተለይም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዜናዊ ጋር ባካሄዷቸው ውይይቶች የኢትዮጵያ መንግስትን አቋም እየተገነዘቡ መምጣታቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በአገሩ የውስጥ ጉዳይ ላይ የማንኛውንም የውጭ ሃይል ጣልቃ ገብነትን በማይፈቅድ መሰረታዊ መርህ ላይ እንደሚመራ ግልፅ የሆነላቸው የአሜሪካው አምባሳደር ከአሜሪካ መንግስታት ጋር ኢትዮጵያን አስመልክቶ የሚለዋወጡት መረጃም የአቋም ለውጥ ማድረጋቸውን ያመላክተ ነበር፡፡

ይህውም አምባሳደር ያማማቶ በኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው የተሾሙበት የስልጣን ዘመናቸው ወደ ማብቃቱ ገደማ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ያደረጓቸውን ውይይቶች አስመልክቶ ለሙያ አጋሮቻቸው ባስተላለፉት መልእክት ላይ ግልፅ አድርገውታል፡፡

እንዲህ በማለት *"ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በግልፅ እንግሊዝኛ የምእራቡን የዴሞክራሲ ፓራዳይም በአፍሪካ ላይ መጫን እንደማይገባ መንግስታቸው በአፍሪካ አገር በቀል ዴሞክራሲ እንዲያብብ እንጂ ከውጭ በተፅእኖ የሚጋት ዴሞክራሲ እንደማይቀበል የገለፁልኝን እኔ በበኩሌ ተቀብየዋለሁ"* ሲሉ ግልፅና ምጥን ባለች ቋንቋ ገልፀውታል፡፡

አምባሳደሩ ከኢትዮጵያ ባለስልጣናት ጋር የሚያካሂዷቸው ውይይቶች በጊዜ ሂደት እየተበራከቱ በመጡ ቁጥር የኢትዮጵያ መሪዎች የአለም ሃያል ነኝ የምትለውን አሜሪካንን ጨምሮ በአገራቸውና በህዝቦቻቸው ሉአላዊነትና ነፃነት ላይ ለሚመጣ ማንኛውም አይነት ጫናና ተፅእኖ የማይንበረከኩ መሆናቸውን ተገንዝበው ነበር፡፡

በመሆኑም አምባሳደሩ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ካካሄዷቸው ተከታታይ ውይይቶች መገንዘብ የቻሉትንና ትክክለኛ መሆኑን ያመኑበትን የሁለትዮሽ ግኑኝነት መርህ እንዲህ ሲሉ ለሙያ አጋሮቻቸው ባስተላለፉት መልእክት አስፍረውታል፡፡

ይህንንም መርህ መቀበላቸውን የሚያመላክተው የኢትዮጵያና የአሜሪካ የሁለትዮሽ ግኑኝነት በምን አይነት መርህ መመራት እንዳለበት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የገለፁላቸውን ባሰፈሩበት የመልእክታቸው ክፍል ነው፡፡

*"እርግጥ ነው አቶ መለስ ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ጋር የተሻለ ግኑኝነት መመስረት ይፈልጋሉ፡፡ይህም ሲሆን ኢትዮጵያ ከራሷ ተነስታ የሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲን በማስፈንና የኢኮኖሚ ልማቷን ባራመደች ቁጥር አሜሪካም ከራሷ ቅድመ ሁኔታ ተነስታ ለኢትዮጵያ በቂ ምህዳር እንድትሰጥ በመፈለግ ጭምር የሚገለፅ ነው"* ሲሉ ነበር ያሰፈሩት ፡፡

አምባሳደር ያማማቶ ከአሜሪካ አዲስ አበባ በደረሱበት ወቅት ያበሳጫቸው የኢትዮጵያ መንግስት ለውጭ ሃይል የሪሞት ኮንትሮል ትእዛዝ አልንበረከክም ባይነት አቋምና መርህ ውለው አድረው ሲያስቡት ትክክለኛ መሆኑን አምነውበታል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት በብሄራዊ ጥቅሙ በሉአላዊነትና በነፃነቱ ላይ የማንንም የውጭ ሃይል ትእዛዝ የማይቀበልና ተንበርካኪ እንዳልሆነ ሲረዱ አሜሪካ ከዚህ መንግስት ጋር ልትመሰርተው የሚገባ ግኑኝነት በእኩልነት በውይይትና በምክክር ላይ የተመሰረተ መሆን ሊሆን እንደሚገባው ራሳቸው አምነው ሌሎች የስራ አጋሮቻቸውን ግንኙነቱን በዚህ መርህ ሊቃኙት እንደሚገባ የሚያሳምኑ መልእክቶችን ማስተላለፍ ቀጠሉ፡፡

የሁለቱ አገራት ግኑኝነትን አስመልክቶ የአሜሪካ መንግስት ባለስልጣናት የተከተሉት አካሄድ በወቅቱ ለተፈጠረው አለመግባባት መንስኤ መሆኑን አምባሳደር ያማማቶ ሲገነዘቡ የመንግስታቸው ከፍተኛ ሃላፊዎች የግኑኝነቱን ማእቀፍ ትክክለኛ በሆነው አቅጣጫ እንዲያስተካክሉ መምከራቸው አስተዋይነታቸውንና አርቆ አሳቢነታቸውን ያረጋገጠ ነበር፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የአሜሪካና

የኢትዮጵያ የሁለትዮሽ ግኑኝነት የሚመራበትን መርህ አስመልክቶ በውይይታቸው ወቅት የገለፁላቸውን መልእክት እንዳለ በማስተላለፍ፡፡

በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እውን የሚሆነው የኒዮ ሊበራል ሃይሉ በማስገደድ ዋጡ የሚለውን ክኒን በመዋጥ እንዳልሆነ መግለፃቸውን አምባሳደሩ ተቀብለውታል፡፡

ይልቁንም የአፍሪካ መንግስታት ከአገሮቻቸውና ከህዝቦቻቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አገናዝበው ለሚቀርፁትና ተግባራዊ ለሚያደርጉት የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ምእራባውያን ትክክለኛነት እውቅና እንዲሰጡ የሰነዘሩላቸውን ሃሳብም እንዲሁ፡፡

ይህንንም በማድረግም አምባሳደሩ የሁለቱ አገራት ግኑኝነትን ወደ ትክክለኛውና ወደ ነበረበት የቀድሞው ሁኔታ እንዲመለስ ማድረግ ችለዋል፡፡

የአገሬ ሰው እንደ መድረክ አመራሮች ካለፉት ሁኔታዎች ትምህርት መቅሰምና ተሞክሮ መውሰድ ያቃተውን ሰው "ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭና አድሮ ቃሪያ" እንደሚለው ሁሉ ዛሬም በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የማንንም ጣልቃ ገብነትን የማይፈቀደውን የኢትዮጵያ ስርአት መርህ የዘነጉት እነዚህ ያረጁና ያፈጁ የመድረክ አመራሮች ግን የአሜሪካን የእንግሊዝንና መሰል ምእራባውያን ሃይል በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገቡ ዛሬ ድረስ ሲወተውቱ ይገኛሉ፡፡ ወደፊትም እንዲህ ይቀጥላሉ፡፡

የመድረክ አመራሮች የውጭ ሃይሎችን በአገር ውስጥ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዲገቡ መማፀናቸውን አዘውትረው የሚያከናውኑት የምርጫ ወቅት ሲቃረብ ይሁን እንጂ እንደ አስፈላጊነቱ ሌላም ጊዜ ቢሆን ይህን ከማድረግ የተቆጠቡበትን ጊዜ በበኩሌ አላስታውስምና፡፡

የመድረክ አመራሮች የውጭ ጣልቃ ገብነትን እየደጋገሙ ሲጋብዙ የሚስተዋሉት ከወቅታዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር እንዲራመዱ በማይፈቅድላቸው አመለካከታቸውና መርሃቸው ሳቢያ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት እንዲህ እንዲያደርጉ ስላስገደዳቸው አይደለም፡፡

ሆኖም እንወክለዋለን የሚሉትን የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት አውቆና ተገንዝቦ በዚህ መርህ የመንቀሳቀስ ተነሳሽነቱና ፍላጎቱ ቢኖራቸው መገኛቸው የኢትዮጵያ አብላጫው ህዝብ በሚገኙባቸው የገጠር አካባቢዎች እንጂ በአዲስ አበባ የውጭ ኤምባሲዎች ባልሆነ ነበር፡፡